*መስከረም 4 ቀን 2001 ዓ.ም*

# ኢትዮጵያዊነት! 152 ቀን በወያኔ የጨለማ ጉድጓድ ውስጥ!

*ከ ኢያልነሽ*



## ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) ይፈታ!
## ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) ይፈታ!
## ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) ይፈታ!

*ሚያዚያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም ዝነኛውና ወጣቱ ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) በወያኔ አገዛዝ በቂም የሐሰት ክስ ተመስርቶበት፣ በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ እየማቀቀ ይገኛል። ቴዲ በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ያላግባብ ታስሮ ፍዳ ሲቆጥር፣ እነሆ ዛሬ ልክ 152ኛ ቀኑን ይዟል። በኢትዮጵያ ፍትህ ተጨራምታ እያዝች፣ ሰብዕና ረክሶ ሽዎችን ባሻትና ባሰኛት ቀን ልፋ በመውሰድ፣ ብዙዎችን የት እንዳደረሰች አልታወቀም። የቴዲም እጣ ፋንታ ይሄው ሆኖ የዘመኑ ልዑላኖች ቀንበጦችን፣ አዛውንቶችንና አእሩጎችን እየጠለፉ ሲቀረጥፉና መዳረሻቸውን ሲያጠፉ፣ 17 ዓመት አደረጉ። ለእነርሱ 17 ዓመቱ ኢትዮጵያን ለማጥፋት አልበቃምና የሠፈረባቸው ዛርና ጅኒ የዋዛ ባለመሆኑ የምንከፍለው የሰው ግብር አንሶት፣ እስካሁን ሊታረቀን አልቻለም። ይልቁንም እብሪትን አርግዞ አገርና ሕዝብን አስጨንቆ ይዟል። ታዲያ ይህንን ዘመን ምን ትሉታላችሁ ወገኖቼ ? እኔ የምለው ዘመነ ጉግማንጉግ። እግዚኦ! ማህረነ!*

*የወያኔ አገዛዝ አሁን በሸኘነው 2ሺህ ዓ.ም ላይ ሚሊዮኖችን እያስራበ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በማፍሰስና በመርጨት "ዕርቀ-ሚሌኒየም" ብሎ ከቢዮንሴና ከሌሎች የውጭ አገር ዘፋኞች ጋር በልዩ አዳራሽ፣ ከፈረንጆችና ከውጭ ከገቡ ኢትዮጵያውያኖች ጋር ሆኖ ዓመት ሙሉ ዳንኪራ ሲረግጥ፣ ሚሊዮን ረሃብተኞችን ደብቆ አጋድሞ ነበር። በውጭ ዘፋኞችና ከውጭ ከገቡ ኢትዮጵያኖች ጋር ሆነው ሲያቀልጡት የነበረው የግፈኞች (ሚሌኒየም) ሳይገባደድ፣ እነሆ! በረሃብ የሚሰቃዩ የሚሊዮን ህፃናት ዋይታ ለዓለም አስተጋባ። ዓለም የእነኝህን በረሃብ የተጎሳቆሉ ሕፃናትን ምስል ዘርግቶ ለ"ዕርዳታ እንድረስላቸው" ጥሪን ጋበዘ።*

## "ሚሌኒየም"! "ሚሌኒየም" "ሚሌኒየም" የወያኔ ሚሌኒየም።

*በዚሁ ባሳለፍነው 2 ሺ ዓ.ም ላይ ነው እንዲሁ ቴዲ አፍሮም ለዘመን መለወጫ አስቦ "አበባዬ ሆይ!" የሚል አዲስ የሙዚቃ አልበሙን ሲለቅ፣ ሙዚቃው መላ ኢትዮጵያዊያንን አስደመመ። በሌላ በኩል ሊለያዩን ለሚመኙት ከፉ ባላንጣዎቻችን ከፍት እንዳንሆን "ለዓለም ዓለም እንዳይለያየን ዘለዓለም " በማለት ኢትዮጵያኖች እጅ ለእጅ ይበልጥ ተያይዘን ኢትዮጵያን እንታደግ ዘንድ በሙዚቃ፣ መልዕክቱን አበሠረ። ከነቢዮንሴ ጋር በተደበቁ ሚሊዮን ረሃብተኞች ጀርባ ላይ ሆነው ዳንኪራ ሲረግጡ የነበሩትን "የሚሌኒየም"*

ዘመነኞችና ጭፍሮቻቸውን ቴዲ በዚህ የሙዚቃ አጨዋወት ስልቱ ኢመንት አድርጎ አሰየ። ይህ ብቻ አይደለም። ቴዎድሮስ ስርቅርቅ ድምፁን በተዋበ የሙዚቃ መሣሪያ አገናኝቶ "አበባዬ ሆይ" እያለ ሲጫወት ኢትዮጵያዊ የሙዚቃ መሣሪያዎቻችንን ሁሉ ሣይቀር፤ ለእነርሱም (እንደ ሰው) መልዕክቱ እንዲደርሳቸው አድርጎ በቅላፄው አሰውቦ ተማጽኗቸዋል። እባካችሁ! ይላቸዋል የሙዚቃ መሣሪያዎቻችንን! እባካችሁ ዋሽንት፣ ክራር፣ ከበሮም ሆነ ማሲንቆ የምትጫወቱት ለአገርና ለህዝብ ይሁን ብሎ በሙዚቃው ያሽሞነሙናቸዋል። እንዲህ በማለት

አበባዬ ሆይ! አበባዬ ሆይ!
ባልነጀሮቻ ቁሙ በተራ
እንጨት ሰብሬ፣ ቤት እስክሠራ፤
እንኳንና ቤት የለኝም አጥር ፤
እደጅ አድራለሁ ኮከብ ስቆጥር።

ሆ! በል ማሲንቆ ሆ በል ክራሬ፣
ዝፈን ለህዝቤ፣ ዝፈን ለአገሬ።
ሆ! በል ዋሽንቴ አንተ ማሲንቆ፣
ስታይ ሰው ታርቆ።

ይልና በሌለ ሠላም፣ በሌለ ፍቅር እንዳይዘፍኑ ይማጸናል የቴዲ የሙዚቃ ጥሪ። እንኳንስ ሰው ዋሽንት ክራርና ማሲንቆ ለሀገር ደህንነትና ለህዝብ የተረጋጋ ኑሮ እንዲጫወቱ አደራውን ጭምር አስተላልፏል። ታዲያ ይህን የመሰለ አንደበት በቃሊቲ እስር ቤት ታስሮ 152 ቀን ሲያስቆጥር እስከመቼ በከንፈር መጠጣ አሴቶቻችንን ለበላዒ ሰብ እየገበርን እንኑራለን! ዝምታስ እስከ መቼ?!



ወያኔ ያሰረው ቴዲን ሳይሆን **ኢትዮጵያዊነትን** ነው፤ ስለዚህ፥ አዎ !ቴዎድሮስ ካሳሁን መፈታት አለበት።

ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ ይፈታ)
ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ ይፈታ)
ቴዎድሮስ ካሣሁን ( ቴዲ አፍሮ ይፈታ)

ቴዲ! የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት ነው፤ ቴዲ የኢትዮጵያ ህዝብ አሴት ነው፤ ቴዲ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንደበት ነው። ታዲያ አንደበታችን ሲዘጋ አለመጮህ፣ አሴቶቻችን ሲጠፉ አለመፈለግ፣ ንብረቶቻችንን ሲዘረፉ አለመቆጨት ምንን ያመላክታል! በጨለማ እስር ቤት ውስጥ ከሚማቅቁት እስረኞቻችንና አበሰኞችስ፣ የእኛው "ነፃነት" ምኑ ላይ ነው ለታሠሩት ካልጮህን፣ ካልተናገርን፣ ካልተሰለፍን? የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ እስር ቤት መኖር የለበትም፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በፖለቲካ አስተሳሰቡ፣

*አቋሙ፣ ሰው መታሠር፣ መገደል፣ መሰደድ፣ መጋዝ የለበትም ብለን ካልጮህንና ካልታገልን፣ መቸም ቢሆን*
*የሀገራችን ባለቤቶች  ለመሆን አይቻለንም። መልካም አዲስ ዓመት ለኢትዮጵያዊያኖች በሞላ!*

*የህዝብ ድምፅ ይከበር! የታሠሩ የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!*
*ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!*
*ቸር ይግጠመን*

<u>ሴብቴምበር 14/ 2008</u>